ሚያዚያ 24 ቀን 2011
አዲስ አበባ

# 15ኛ አስቸኳይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 15ኛ አስቸኳይ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የባንክ ስራ አዋጅን ለማሻሻል በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ ዋነኛ ዓላማም በአሁኑ ወቅት በሃገር ደረጃ እየተካሄደ ካለው መጠነ ሰፊ የለውጥ ማዕቀፍ አንጻር የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በባንክ ዘርፍ ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ማድረግ ፣ ባንኮች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሃገር ገንዘብ በማሰባሰብ በተለያዩ የልማት ዘርፎች እንዲውል በማድረግ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ለመቃድረግ እና ባንኮች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ የክፍያና የክፍያ አፈጻጸም ስርዓት ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸው በመሆናቸው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኂላ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
2. ከዚህም ሌላ ምክር ቤቱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅን ለማሻሻል በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ ኢትዮጵያ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ዘመናዊና ተደራሽ በማድረግ የንግድ ስራን ለመጀመር ምቹ ሃገር እንድትሆን ስርዓቱን የሚያስተዳድሩ ህጎችን የማሻሻል ስራ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ተወያይቶ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
3. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን በገንዘብ ለመደገፍ ጥቅም ላይ የዋሉ ገንዘቦችን ለማገድ በአዋጅ ቁጥር 1132/2011 አንቀጽ 9 መሰረት በተዘጋጀ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ትዕዛዝ ላይ ተወያይቷል፡፡ አገራችን የሚጠበቅባትን አለም አቀፍ ግዴታ ከመወጣት አንጻር እና አገራችን ከሌላው ዓለም ጋር የምታደርገው ግብይት እና የውጭ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዳይስተጓጎል ለማድረግ እንዲቻል የሠላም ሚኒስቴር ረቂቅ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ትዕዛዝ አዘጋጅቶ ለውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ትዕዛዝ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኂላ ማሻሻያዎችን በማከል በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

4. የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ክፍያዎችን ለመወሰን የቀረበው ረቂቅ ደንብ በምክር ቤቱ የታየው ሌላው አጀንዳ ሲሆን የገንዘብ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ኤጀንሲ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያወጣውን ወጪ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑ ተገልጋዮች እንዲሸፍን ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ ረቂቅ ደንቡን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ውሳኔ እንዳቀረበ ተገልጿል፡፡ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡
5. ምክር ቤቱ የጂኦተርማል ሀብት ልማት ረቂቅ ደንብ ላይም ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ በተፈጥሮው አላቂ የሆነውን የማዕድን ሀብት ለማልማት የተዘረጋው የህግ ማዕቀፍ ታዳሽ ለሆነውና የራሱ የሆነ የተለያዩ ባህርያት ላሉት የጂኦተርማል ሃብት ልማት ብዙም የሚስማማ አለመሆኑን በመግለጽ የውኃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ረቂቅ ደንቡን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በዝርዝር ተወያይቶ ረቂቅ ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡
6. በመጨረሻም ምክር ቤቱ ስለ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ በተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ አገራችን እያስመዘገበችው ካለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እና ይህንኑ ሳይቆራረጥ ለማስቀጠል ሲባል ከተነደፉት የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር የሚጣጣምና በአንድ በኩል ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታና ኢኮኖሚው በቂ ስራ እየፈጠረ ሚዛኑን የጠበቀ የስራ ገበያ ለመፍጠር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለሰራተኞች ምቹ የስራ ሁኔታ የሚፈጥር የህግ ማዕቀፍ መቅረጽ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//